# ሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴዎች አጠቃላይ ትንተና

በባለፈው ጽሁፍ የሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ እና ግብይት መመሪያ አጠቃላይ ይዘት እና የተወሰኑ ክፍሎችን በዝርዝር አይተናል። በዚህ ክፍል ቀሪዎቹን የመመሪያውን ይዘት እንደሚከተለው እንዳስሳለን።

## የጥቅል ምዝገባ፡ ለትላልቅ እና ለተደራጁ አውጪዎች

በመመሪያው እንደተመለከተው የጥቅል ምዝገባ ማለት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው በባለሥልጣኑ በተፈቀደ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እንዲያቀርብ የሚያስችል የምዝገባ መግለጫ ነው። በመመሪያው ከአንቀጽ 25 እስከ 28 የተደነገገው የጥቅል ምዝገባን የሚያቋቁም ሲሆን አውጪዎች በባለሥልጣኑ ተደጋጋሚ ሙሉ ምዝገባ ማድረግ ሳይጠበቅባቸው አንድ ጊዜ ባደረጉት ምዝገባ ብቻ በጊዜ ሂደት ለብዙ ሽያጮች ሰነዶችን ለሽያጭ እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል።

ለጥቅል ምዝገባ ብቁ ለመሆን አውጪው ቢያንስ ለሦስት ዓመታት በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ተመዝግቦ የቆየ፣ ይፋ የማድረግ ግዴታዎችን በአግባቡ የተወጣ፣ የብድር የመመለስ ግዴታዎችን የተወጣ እና የካፒታል ገበያ ህግ ጥሰቶችን ያልፈጸመ መሆን ይጠበቅበታል። ከዚህ በተጨማሪ በጥቅል ምዝገባ የቀረቡት ወይም የሚሸጡት ሰነዶች ድምር ዋጋ አምስት ቢሊዮን ብር ማነስ እንደሌለበት በመመሪያው ተመልክቶ ይገኛል።

ይህ የሚያሳየው የጥቅል ምዝገባ በዋናነት ለትልልቅ እና አቅም ላላቸው ድርጅቶች የተገደበ መሆኑን ነው። የጥቅል ምዝገባ የሚሰራበት የጊዜ ገደብ ያለው ሲሆን አንድ ጊዜ በጥቅል ምዝገባ የተደረገለት አውጪ በህግ የተቋቋሙ አካላት ወይም የብዙሃን ኤጀንሲ ካልሆነ በስተቀር ምዝገባው የሚጸናው ለሶስት አመት ብቻ ነው።

በህግ ለተቋቋሙ አካላት እና የብዙሃን ኤጀንሲ የሚያደርጉት ጥቅል ምዝገባ በባለሥልጣኑ ወይም በራሳቸው በአውጪዎቹ በተቃራኒው ካልተገለጸ በስተቀር ላልተወሰነ ጊዜ ጸንቶ የሚቆይ ይሆናል። በተጨማሪ ጥቅል ምዝገባ የማይታደስ መሆኑ በመመሪያው በግልጽ ተመልክቶ ይገኛል።

አውጪው ጥቅል ምዝገባ ለማድረግ ለባለሥልጣኑ አመልክቶ፣ መስፈርቶቹን አሟልቶ ከተመዘገበ በኋላ እያንዳንዱን አቅርቦት በተመዘገበው ጥቅል ምዝገባ መሰረት ከማቅረብ ወይም ለሽያጭ ከማውጣቱ በፊት የተሻሻለ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት አለበት። የአውጪው ጥቅል የደንበኛ ሳቢ መግለጫ እና በተከታታይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች ባለሥልጣኑ በሚያዘው መልኩ በአውጪው ድህረ-ገጽ፣ ሰነዶቹ በተመዘገቡበት እና በሚገበያዩበት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ድህረ-ገጽ እንዲሁም ለአውጪው የግብይት አገልግሎት በሚሰጡ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ድህረ-ገጽ የፊት ለፊት ገጽ ላይ ታትሞ መውጣት አለበት።

ሌላው የተለዩ ሽያጮች የሚመዘገቡበት አኳሃን በመመሪያው ተደንግጎ ይገኛል። ከእነዚህ
ውስጥ አንዱ በአሁን ወቅት በሕዝብ ተይዘው የሚገኙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የምዝገባ
አስገዳጅነት የሚደነግግ ሲሆን መመሪያው ምዝገባውን የማስተዋወቅ ምዝገባ ብሎ ይጠራዋል።

# ሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴዎች አጠቃላይ ትንተና

ሰነዶቹ በሙሉ ተሸጠው በባለአክሲዮኖች እጅ የሚገኙበት አውጪ አክሲዮኖቹ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ለማስተዋወቅ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ለህዝብ ሽያጭ እንዲደረግ የሚፈልግ ከሆነ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በማዘጋጀት በባለሥልጣኑ ማስመዝገብ መቻል አለበት። በመመሪያው እንደተመለከተው በዚህ የምዝገባ ማመልከቻ ነባር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እንጂ አዲስ ሊካተት እንደማይችል ተመልክቶ ይገኛል። በምዝገባ መስፈርት ደረጃም ቢሆን እነዚህ ሰነዶች ተሸጠው ለባለአክሲዮኖች የተላለፉ በመሆናቸው ምስረታ ላይ ለሚገኙ አውጪዎች የተቀመጡ እንደ የድልድል ፖሊሲን ግልጽ አድርጎ የማቅረብ ግዴታ በእነዚህ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

የደንበኛ ሳቢ መግለጫ እንዲያቀርቡ የማያስፈልጋቸው ወይም ከምዝገባ መስፈርቶች ነጻ የተደረጉ አውጪዎችን በተመለከተ እነዚህ አውጪዎች ለባለሥልጣኑ የሚያቀርቡት የምዝገባ መግለጫ ስለአጠቃላይ አቅርቦት እና ድልድል ይዘት፣ አስፈላጊነት እና ምክንያት፣ የወጡትን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አይነት እና ቁጥር የሚገልጽ የመረጃ ማስታወሻ ከወጣው የሰነድ አቅርቦት ጋር በሰነድ ማስረጃ ተደግፎ ማቅረብ ለምዝገባ በቂ መሆኑ በመመሪያው ተመልክቷል።

ሌላው የአውጪው የጉርሻ አክሲዮኖች በባለሥልጣኑ የሚመዘገቡበት ሁኔታ ነው። እንደሚታወቀው የጉርሻ አክሲዮን ማለት የአንድ ድርጅት ባለአክሲዮኖች ባለቸው የአክሲዮን ድርሻ መጠን ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ የሚከፋፈሉ የአውጪው አክሲዮኖች ናቸው። ታዲያ እነዚህን የጉርሻ አክሲዮኖችን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻን በተመለከተ ምን ምን ማሟላት እንዳለባቸው ተመልክቷል።

እነዚህም የአውጪው የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ፣ ስለጉርሻ አክሲዮኖች እንዲወጡና በባለስልጣኑ እንዲመዘገቡ ያሳለፈው ውሳኔ የቃለ–ጉባኤ ቅጂ፣ የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የጉርሻ አክሲዮኖች የተፈቀዱበት እና በባለሥልጣኑ ምዝገባ እንዲደረግ ያሳለፉት ውሳኔ ቃለ–ጉባኤ ቅጂ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ተሟልተው ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለባቸው። ባለሥልጣኑ የጉርሻ አክሲዮኖችን ምዝገባ ከመፈጸሙ በፊት ምዝገባውን የጠየቀው አውጪ ምዝገባ በጠየቀበት ጊዜ ከነበረው መጠባበቂያ ፈንዶች ወይም ከትርፍ ላይ ለጉርሻ አክሲዮኖቹ ክፍያ እንዲሆን ታስቦ የተቀመጠ ገንዘብ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት።

ሌላው ስለተለዋጭ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ነው። ተለዋጭ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማለት በአውጪ እና በገዥ መካከል በሚደረግ ስምምነት አውጪው ከገዥው የሚወስደውን ብድር በተወሰነ ጊዜ መመለስ ካልቻለ ወይም ደግሞ በፈቃደኝነት ብድሩን ወደ አክሲዮን ለመቀየር የሚስማሙበት ሁኔታ ነው። የተለዋጭ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባ በተመለከተ በአውጪ እና በሌላ አካል መካከል በተደረግ ስምምነት የብድር ሰነድ ወደ አክሲዮን የሚለወጥ ከሆነ ለውጡ በተደረገ በሰላሳ ቀናት ውስጥ በባለሥልጣኑ መመዝገብ አለበት።

አውጪው ለምዝገባ የሚከተሉትን የሚያሳይ የመረጃ ማስታወሻ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት። እነዚህም የተለዋጭ የብድር ሰነድ ሙዓለ ንዋይ ስምምነት ዋና ዋና ነጥቦች፣ የሚለወጠውን መጠን፣ የሚለወጥበትን ምክንያት፣ የአውጪው፣ የገዥው እና የአዲስ የሚወጣው አክሲዮን ባለቤት

# ሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴዎች አጠቃላይ ትንተና

ስም፣የአውጪውን ካፒታል የሚያሳይ መረጃ (የተከፈለ እና የተፈረመ)፣ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ የሚቀየሩባቸው የአክሲዮን አይነቶች እና ተያያዥ መብቶች፣ የአውጪው ካፒታል፣የአክሲዮን መዋቅር እና የእዳ አቋም ላይ የሚያስከትለው ውጤት የሚያሳዩ መሆን አለባቸው። በተጨማሪ የተለዋጭ ብድር ሰነድ ለማስመዝገብ በኩባንያው ዋና ጸሃፊ የተፈረመ የስምምነቱ ቅጂ፣ ጉዳዩን በተመለከተ የተለዋጭ የብድር ሰነድን ለማውጣት የተወሰነ የቦርድ ውሳኔ መግለጫ፣ ካፒታል ለማሳደግ እና የዕዳ ሰነድ ለማውጣት በባለአክሲዮኖች ልዩ ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነበት ቃለ-ጉባኤ ቅጂ፣ በስምምነቱ መሰረት የተከፈለ ክፍያ ማስረጃ፣ እና ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸው ማስረጃዎች ተሟልተው መቅረብ እንዳለባቸው በመመሪያው ተመልክቷል።

## ለሽያጭ የማቅረብ ሂደት

### የግብይት አማካሪ መሾም

አውጪዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከማስመዝገብ አንጻር ከባለሥልጣኑ የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች ለማሟላት በጥሩ አቋም ላይ የሚገኝ የግብይት አማካሪ መሾም አለባቸው። አማካሪው ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የቁጥጥር ተገዢነትን ማረጋገጥ፣ ስለግዴታዎች ለዳይሬክተሮች ማሳወቅ፣ የምዝገባ መግለጫ ዝግጅትን ማስተባበር፣ ሰነዶችን ማስገባት፣ ለባለሥልጣኑ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት እና በአቅርቦቱ ወቅት እና በኋላ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርቶችን ማቅረብ የሚሉት ይገኙበታል።

ይህ መስፈርት የኢንቨስተር ጥበቃ ሥራዎችን የሚደግፍ ሲሆን የግብይት አማካሪው አውጪው ያለባቸውን መሰረታዊ መረጃዎች ይፋ የማድረግ ግዴታ ሳይወጣ የመቅረት እድልን ከመቀነስ ባሻገር የቁጥጥር ጥሰቶች የመከሰት እድልን ያስቀራል። በዚህ ረገድ እንደ ግብይት አማካሪ የሚሰሩትን ፈቃድ ያላቸው የኢንቨስትመንት ባንኮችን እና ሌሎች ብቁ አማካሪዎችን መሾም ሊፈጠሩ የሚችሉ አደጋዎችን ይቀንሳል።

### የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ማፅደቅ

በመመሪያው ላይ አውጪው በባለሥልጣኑ የተፈቀደለት ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ከሌለ በስተቀር ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ሽያጭ ማቅረብ እንደማይቻል ተቀምጧል። በመርህ ደረጃ ከምዝገባ ውጪ የሚደረግ ለህዝብ ማቅረብ የሚከለክል ቢሆንም በልዩ ሁኔታ ከምዝገባ ነጻ የተደረጉ ወይም የተፈቀደላቸው አውጪዎች መኖራቸው ተመልክቷል። እነዚህም በአንቀጽ 35 የተመለከቱት ለተወሰኑ በተመሳሳይ መደብ ያሉ ነባር አክሲዮኖችን ለመተካት የወጡ አክሲዮኖች ሲሆኑ እና አዲሱን አክሲዮን ማውጣት የአውጪውን ካፒታል የማያሳድግ ሲሆን፣ የአውጪውን ሌሎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በመቀየር የተገኙ አክሲዮኖች ሲሆኑ እና ነባሮቹ ከዚህ በፊት ወጥተው የተመዘገቡ ሲሆኑ፣ አውጪው ለሰራተኞቹ የሚያደርግላቸው የአክሲዮን አቅርቦት እና ድልድል፣ ከምዝገባ መስፈርቶች ነጻ ናቸው።

# ሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴዎች አጠቃላይ ትንተና

የደንበኛ ሳቢ መግለጫው በቀላሉ ለመረዳት የሚቻል፣ በተገቢው ርዕስ ስር የቀረበ እና ከድብቅ አቀራረብ የጸዳ መሆን አለበት። ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ኢንቨስተሮች በመረጃ ላይ ለተመሰረቱ የኢንቨስትመንት ውሳኔዎች እንዲያደርጉ ለማስቻል የሚያስፈልጋቸውን ሁሉንም መረጃዎች ማግኘት እንዲችሉ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ማሟላት ስላለባቸው ይዘት እና ቅርጽ መስፈርቶች የተወሰነ ደረጃን ያስቀምጣል። በዚህ ረገድ በደንበኛ ሳቢ መግለጫ የሚካተቱ መረጃዎች አንድ ምክንያታዊ ኢንቨስተር የአንድን አውጪ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለመግዛት በምክንያታዊነት የሚጠይቋቸው መረጃዎች ሁሉ ማካተት አለበት። በተጨማሪ ባለሥልጣኑ በደንበኛ ሳቢ መግለጫ እንዲካተቱ የሚያዛቸው መረጃዎች የአውጪውን የስራ ባህሪ እና የሚያወጣቸውን ሰነዶች አይነት ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንደሚገባ በመመሪያው ተመልክቶ ይገኛል።

በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ የተካተቱ የትርፍ ወይም የገቢ ትንበያዎች ወይም ማናቸውም የወደፊት ሁኔታ አመላካች መግለጫዎች እና ግምቶች በበቂ ማብራሪያ ወይም የፍሬ ነገር መሰረት ተደግፎ መቅረብ አለባቸው። በዚህ መልኩ የሚቀርቡ መረጃዎች በበቂ ማብራሪያ መደገፍ ካልቻሉ መቅረብ እንደሌለባቸው ተመልክቷል። በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ የተካተተ የአውጪው ሂሳብ መግለጫ ኦዲት ያልተደረገ ወይም በገለልተኛ ኦዲተር ያልተሰራ ከሆነ ይህንኑ በግልጽ ማሳየት ያስፈልጋል።

## የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ማፅደቅ

መመሪያው በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ላይ ስለተመለከቱ የአውጪው መረጃዎች ትክክለኝነት ኃላፊነት ስለሚኖርባቸው ሰዎች የአንድነት እና የተናጠል ተጠያቂነቶችን ያስቀምጣል። የአውጪው ሁሉም ዳይሬክተሮች (ዳይሬክተር ለመሆን የሚስማሙትን ጨምሮ)፣ አውጪው ምስረታ ላይ ያለ አዲስ ድርጅት ከሆነ አደራጆቹ፣ በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ስሙ ተጠቅሶ ኃላፊነት ለመውሰድ የተስማማ ማንኛውም ሰው፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዩን የሚያቀርበው አውጪው ሳይሆን አቅራቢው ሲሆን የአቅራቢው የቦርድ አባላት በሙሉ በአንድነት እና በተናጠል ኃላፊነት አለባቸው። በዚህ ረገድ እነዚህ የተጠቀሱት ኃላፊነቶችን ወደጎን ለማድረግ ወይም ለማቅለል የሚደረግ ስምምነት ዋጋ እንደማይኖረው በመመሪያው በግልጽ ተመልክቷል።

## የከፍተኛ ባለሙያ መግለጫዎች

በመመሪያው አንቀጽ 39 መሰረት የተሰጠ የከፍተኛ ባለሙያ መግለጫ ካለ የባለሙያው መግለጫ በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ ከመካተቱ በፊት ባለሙያው የጽሑፍ ፈቃድ የሰጠ መሆኑን እና እንዳልሰረዘው የሚገልጽ ወይም በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት። ይህ በሚሆንበት ጊዜ በአግባቡ የባለሙያው ልምድ፣ ብቃት እና ሌሎች የትምህርት ዝግጅቶች መኖራቸው መካተት አለበት። ይህ ሂደት ኢንቨስተሮች የባለሙያዎችን ብቃት እና ተዓማኒነት እንዲገመግሙ ያስችላቸዋል።

ሌላው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ቢሆንም መረጃዎቹ የሕዝብ ጥቅም የሚጻረሩ ከሆነ ወይም ለአውጪው ጥብቅ ስጋት ከሆኑ እና መረጃው ቀሪ መደረጉ ጉዳት ሌለው ከሆነ፣ ጠቃሚነቱ ዝቅተኛ ከሆነ፣ ወይም ምንም ተጽዕኖ የሌለው ነው ብሎ ባለሥልጣኑ ካመነ ይፋ እንዳይደረጉ ሊፈቅድ ይችላል።

# ሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴዎች አጠቃላይ ትንተና

የ

የደንበኛ ሳቢ መግለጫው ከመጽደቁ በፊት በማንኛውም መልኩ በአውጪው ላይ ጉልህ ለውጥ ከተፈጠረ ወይም በቀረበው መረጃ ላይ ስህተቶች ከተገኙ የሚታረሙበትን አግባብ መመሪያው አካቷል። በዚህ ረገድ ደንበኛ ሳቢ መግለጫው ለባለሥልጣኑ ከቀረበ በኋላ በአውጪው ድርጅት ውስጥ ጉልህ ወይም መሰረታዊ ለውጥ ቢከሰት ወይም በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ውስጥ ስህተት ቢገኝ እና ስህተቶቹ በደንበኛ ሳቢ መግለጫ የተካተቱትን መሰረታዊ ጉዳዮችን በቂ ያልሆኑ፣ አሳሳች፣ እውነተኛ ያልሆነ ከሆነ አውጪው ስህተቱ በታወቀ በአስር ቀናት ውስጥ ለውጡን የሚያሳይ ማሻሻያ በማድረግ የተሻሻለውን የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ከትክክለኛ ማስረጃ እና ደጋፊ ሰነዶች ጋር በማድረግ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።